ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

ሐምሌ 1999 ዓ.ም. የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች ቁጥር 8

# የፍልሰት፣ ግጭትና መፈናቀል ትስስር

- የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡
- የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡
- በአዲስ አበባ (በ97.1 ሞገድ) እና በአዋሳ (በ100.9 ሞገድ) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፡፡
- በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን ያካሂዳል፡፡
- በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን፡፡

## 1. መግቢያ

እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ኋላቀር ሀገሮች የኢኮኖሚው መሠረት ግብርና በመሆኑ የብዙዎች ህይወት የሚወሰነው መሬትንና መሠል የተፈጥሮ ሀብትን ለመጠቀም በሚኖራቸው አቅም ላይ ነው፡፡ ይህ አቅም ደግሞ በድህነቱና ሌሎች ተዛማጅ ምክንያቶች የተነሳ እጅግ ውስን በመሆኑ ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ የመጋለጥ እድሉ ሰፊ ይሆናል፡፡ እንዲህ አይነት ክስተቶች ሲፈጠሩ ሰዎች ከአደጋ ራሳቸውን ለመታደግ ከትውልድ ስፍራ መፍለስን ጨምሮ የተለያዩ አማራጮችን ይወስዳሉ፡፡

ሰዎች የትውልድ ሥፍራቸውን የሚቀያየሩባቸው በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም የመሬት መጎዳት፣ የአፈር መሸርሸር፣ የደን መራቆትና የአየር መዛባት፣ የዝናብ ዕጥረትና ተደጋጋሚ ድርቅ ወዘተ.. በአጠቃላይ የአካባቢ ሁኔታ ለኑሮ ምቹ ያለመሆንና የድህነት መባባስ ለፍልሰት ዋነኛ መንስኤ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ በፍልስት የትውልድ ሥፍራቸውን የሚለቁ ሁሉ ድሆች ናቸው ለማለት ያስቸግራል የድህነት መነሻው ሰው ሰራሽ ችግሮችንም ያካተተ ነውና፣ ለምሳሌ የሰው ልጅ አብሮ በመኖር የሚያካብታቸው የማህበራዊ ዕሴቶች መላላትና መፍረስ፣ በዘርና በሀይማኖት መከፋፈልና ይህንኑ ተከትሎ በሚፈጠሩ የጥላቻ ስሜቶች ምክንያት ግጭቶች ሊከሠቱ መቻላቸው ለመፈናቀልና ፍልሰት መንስኤዎች ይሆናሉ፡፡ ለተሻለ ህይወት ፍለጋ የሚደረግ ፍልሰትም ሌላው መንስኤ ነው፡፡

የሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ከላይ ለተገለፁት እንደ አፈር መሸርሸር፣ የዝናብ እጦትና ተደጋጋሚ ድርቅ የተጋለጠ በመሆኑ የገጠሩ ነዋሪ የትውልድ ሥፍራውን እየለቀቀ ሻል ባሉና ጫና ባልበዛባቸው አካባቢዎች ለመስፈር ተገዷል፡፡ ነዋሪው ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ አደጋዎችን ለመቋቋም በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት የሚፈልስ ሲሆን ለዚህ ፅሁፍ መነሻ የሆነው ጥናት የሚያተኩረው በምስራቅ ወለጋ ልዩ ስፍራው ጊዳ ኪረሙ ወረዳ ላይ በተደጋጋሚ በተደረገው ግብታዊ ፍልሰትና ሰፈራ ላይ ነው፡፡ ሰፋሪዎቹ በአብዛኛው ከአማራ ክልል የተለያዩ ዞኖችና ወረዳዎች የትውልድ ስፍራቸውን እየለቀቁ የፈለሱ ሲሆን ኋላ ላይ በተፈጠሩ ችግሮች ለዳግም ስደት ተዳርገዋል፡፡ በጊዳ ኪረሙ ወረዳ ተደጋግሞ የተካሄደው ሰፈራ በሰፋሪውና በነባሩ ተወላጅ መካከል መቻቻል እንዲጠፉና ወደ ግጭት የሚያመራ ክስተት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡

## 2. የጥናቱ ዓላማ:-

- ከአማራው ክልል የትውልድ ስፍራ ወደ ኦሮሚያ ክልል ምስራቅ ወለጋ ዞን በተደጋጋሚ የተደረገው ፍልሰት መንስኤዎችን መለየት፣
- ሠፈራው በተካሄደበት ቦታ ላይ ሰፋሪው ኑሮውን ያመቻቸባቸው ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ትስስሮችን በመፈተሸ ቀጥሎ ለተከሰተው ግጭት መንስኤዎችን ማጥናት፣
- በስፍራው ተከስቶ ለሞትና ለመፈናቀል ላበቃው ግጭት መሠረታዊ ምክንያቶችን መለየት፣
- ተመሳሳይ ችግሮች እንዳይፈጠሩ መወሰድ ያለባቸውን ዕርምጃዎች አስመልክቶ የፖሊሲ ጠቋሚ ሀሳቦችን ማቅረብ፡፡

## 3. የመረጃ ምንጭና የጥናቱ ዘዴዎች:-

ጥናቱ የተካሄደው የመጀመርያ ደረጃ መረጃዎችን ጉዳዩ በቀጥታ ከሚመለከታቸው ባለጉዳዮች ጋር በፅሑፍና በቃለ-መጠይቅ እንዲሁም የቡድን ውይይቶችን በማካሄድ ነው፡፡ መረጃዎችን ለማጠናከር ይረዳ ዘንድም በግጭቱ የተሳተፉ ወይም የተጎዱትን ብቻ ሳይሆን የአካባቢውን የኦሮሞ ተወላጆችና ኑሮአቸውን ቀደም ሲል በአካባቢው የመሠረቱ ሰፋሪ አማራዎችንም አጥኚው አወያይቷል፡፡ ከቡድንና የግል ውይይት በተጨማሪ 180 የሚሆኑ የተፈናቀሉ ሰፋሪ አባወራዎች ቃለመጠይቁን ሞልተዋል፡፡ እንዲሁም ጥናቱ በምሥራቅ ወለጋ ዞን፣ በጊዳ ኪረሙ ወረዳ፣ በአማራ ክልል እና በአዊ ዞን የሚገኙትንና ጉዳዩ የሚመለከታቸውን የመንግሥት ባለሥልጣናትና የሥራ ኃላፊዎችን አካትቷል፡፡

## 4. የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች:-

### ሀ) የፍልሰቱ መንሥኤና ሠፈራው

እንደ ጥናቱ ውጤት ወደ ምስረቅ ወለጋ ጊዳ ኪረሙ ወረዳ ፍልሰት መካሄድ የጀመረው እ.ኤ.አ. ከ1940ዎቹ ጀምሮ ቢሆንም እጅግ የተደጋገመው ግን ካለፉት

ሦስት ዓሥርት ዓመታት ወዲህ ነው:: ብዙዎቹ ሰፋሪዎች ከደቡብ ጎንደር፣ ከደቡብ ወሎ፣ ከምስራቅና ምዕራብ ጎጃም የፈለሱ ናቸው::

ለዚህ ፍልሰት ዋነኞቹ ምክንያቶች ናቸው ተብለው ሊጠቀሱ የሚችሉት የመሬት መሸርሸር፣ የአየር መዛባት፣ የሕዝብ ብዛት ጫና፣ ድህነት፣ የተፈጥሮ ሀብትን በአግባቡ ለመጠቀም ያለመቻል፣ የአደጋ ተጋላጭነት፣ የምግብ ዋስትና ያለመኖር፣ ወዘተ ናቸው:: በሌላም በኩል ቀደም ብለው ፈልሰው ኑሮአቸውን የመሰረቱ ሰፋሪዎች የተሻለ ሁኔታ መኖሩን ለቀሪዎች የሚናገሩ መኖራቸውም የቤተሰብና የጓደኛ ጫና ለሚፈጥረው ፍልሰት አስተዋፅኦ አድርጓል::

ሰፋሪዎቹ ጊዳ ኪረሙ እንደደረሱ ቀድመው በስፍራው ከደረሱት ሰፋሪዎችጋ በመጠጋት በጉልበት ሥራ እንዲሁም በጋርዮሽ የእርሻ ሥራ ላይ ይሰማራሉ:: ከዛም አካባቢውን ሲለምዱ በተለያዩ መንገዶች የራሳቸውን የእርሻ መሬት ይይዛሉ:: በጥናቱ ውጤት መሠረት ቃለ መጠይቅ ከተደረገላቸው ሰፋሪዎች ውስጥ ግማሽ ያህሉ መሬት የያዙት ከአካባቢው ነዋሪዎች ጋር በሚያደርጉት የኮንትራት ውል ሲሆን ሀያ አምስት በመቶ ያህሎቹ ደግሞ በግዢ ካገኙ በኋላ ጫካዎችን በመመንጠር ደን የነበረባቸውን ቦታዎች ወደ እርሻ መሬትነት በመቀየር ነው::

ከላይ በተጠቀሰው ሒደት ሰፋሪዎቹ ኑሯቸውን በማመቻቸት በአስራ ሶስት የገጠር ቀበሌዎች በስፋት ሰፍረው የሚገኙ ሲሆን በአካባቢው ተወላጅ እምብዛም ባልተያዙ ቆላማ ቦታዎች ላይ እንዳተኮሩ ተስተውሏል:: ከአጠቃላይ መረጃዎችና በአጥኚውም ዕይታ ሰፋሪዎቹ በሶስት የተለያዩ ጊዜያትና ሁኔታዎች ወደ ጊዳ ኪረሙ የፈለሱ ናቸው:: ይኸውም አንደኛ በንጉሱ ዘመን የኦሮሞ ባላባቶች ፓርላማ ለመመረጥ፣ ሰፊ መሠረት ለማግኘትና የታክስ መሠረትም ለማስፋፋት አማራውን ሰፋሪ ያበረታቱ ስለነበር@ ሁለተኛ እ.ኤ.አ. በ1975 ዓም በተካሄደው የመሬት አዋጅ በርካታ መሬት ከፊውዳል ባላባቶች እጅ መውጣት እንደ አንድ መስህብ ማገልገሉ@ ሶስተኛ እ.ኤ.አ. ከ1995 ዓ.ም. ወዲህ የቡሬ ለቀምት መንገድ በመከፈቱ ለእንቅስቃሴና ለመረጃ ልውውጥ አመቺ ሁኔታ መፍጠሩ ዋና ዋናዎቹ ናቸው:: በዚህም መሰረት ሰፋሪዎቹ በንጉሱ ዘመን የሰፈሩ @ በ1984/85 የተከሰተን ድርቅ ተከትሎ በወረዳው በተደረገው የመልሶ ሰፈራ ፕሮግራም የተካተቱ (ጥናቱ ይህን አላካተተም) ፣ እ.ኤ.አ. በ1991 ዓ.ም በተደረገው የመንግስት ለውጥ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ወረዳው የገቡና እ.ኤ.አ. በ1997/98 ዓ.ም. በተደረገው የአማራ ክልል የመሬት ክፍፍል በተለይም ቋሪት በተባለው የጎጃም ወረዳ ይዞታቸውን በማጣት የፈለሱ ናቸው::

### *ለ) ማህበራዊ ትስስርና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ*

እንደ አካባቢው ተወላጆችና ሰፋሪዎች አመለካከት ለበርካታ አሥርተ አመታት በስፍራው የቆዩት አማራ ስፋሪዎች ከኦሮሞ ተወላጆች ጋር በጋብቻ፣ በክርስትና አባትነትና እናትነት፣ ልማዳዊና ሀይማኖታዊ ትስስር፣ በአበልጅነት፣ ወዘተ. ተዋህደው ኖረዋል:: ከጥቂት ዓመታት ወዲህ ወደ ሥፍረው የሔዱት ሰፋሪዎች ግን እምብዛም በማህበራዊ ትስስሩ ያልገፉበት መሆናቸው ይነገራል:: ባጠቃላይ የሰፋሪዎቹ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ሲታይ ከትውልድ ስፍራቸው በተሻለ መልኩ መኖራቸውን ሰፋሪዎቹ ራሳቸው ይናገራሉ:: ለምሳሌ ቃለመጠይቅ ከሞሉት 180 ሰዎች መካከል በትውልድ ቦታቸው ከአንድ በላይ የቀንድ ከብት የነበራቸው ስልሳ ዘጠኝ በመቶ ሲሆኑ ጊዳ ኪረሙ መኖር ከጀመሩ በኋላ ግን 96 በመቶ ደርሰዋል:: አንዳንድ ቤተሰቦችም እስከ 30 የሚደርሱ ከብቶች እንደነበራቸው ተገልፆአል:: በተጨማሪም የአካባቢው ነዋሪዎችና የመንግስት ኃላፊዎች ሰፋሪዎቹ የመጡበትን ሁኔታ ሲገልጹ ከድህነቱና የአካባቢው መጎዳት በተጨማሪ በትውልድ ስፍራቸው በወንጀል ክስ ተመስርቶባቸው የፍርድ ሒደቶችን ሸሽተም የፈለሱ እንዳሉ ይናገራሉ:: ይህ ግን ባጥኚው በማያወላዳ ሁኔታ ሊረጋገጥ አልቻለም::

### *ሐ) ግጭትና መፈናቀል*

በኢትዮጵያ ውስጥ በተለያዩ ማህበረሰቦች መካከል ለሚነሱ ግጭቶች መንስኤ በመሆን ከሚታወቁት ምክንያቶች ውስጥ በተፈጥሮ ሀብት በተለይም በመሬት በውሀና በግጦሽ ሳር ያለመግባባት፣ በድንበር አከላለል ያለመርካት፣ በቋንቋ አጠቃቀም፣ የአጎረባች ሥፍራዎችን የይገባኛል ጥያቄና የመሳሰሉት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው::

በተመሳሳይ ሁኔታ በጥናቱ አካባቢ ለደረሰው ሞትና መፈናቀል ምክንያት የሆነው የመጀመርያ ግጭት የተጫረው በመጋቢትና ሚያዝያ ወራት 1992 ዓ.ም. ሲሆን ቀደም ሲል በሁለቱ ማለትም በአማራ ሰፋሪዎችና በኦሮሞ ተወላጆች መካከል የተደረጉ የመሬት የኮንትራት ውሎች መፍረስ፣ የደኖች መጨፍጨፍ፣ የቦታ ስሞች ወደ አማርኛ መለወጥ፣ የሰፋሪዎቹ መሳርያ መታጠቅና በአካባቢው ልዩ የአማራ ዞን እንዲሰየም በሰፋሪዎቹ ዘንድ እንደነበረ የሚነገረው ፍላጎት ተደማምሮ ወደ ግጭት ማምራቱን ጥናቱ አሳይቷል:: በሰፋሪዎቹ ወገን ግን ዋኛው መንስኤው የካድሬዎቹ ፀረ-አማራ ቅስቀሳ እንደሆነ በዓፅንኦት ይጠቀሳል::

የመጀመርያው ግጭት በሁለቱም ወገን የሽማግሌዎች ግልግል ሲበርድ ሁለተኛውና ከአምስት ወራት በኋላ እንደገና የተቀሰቀሰው ግጭት ሰዎችን ለሞትና ለመፈናቀል ዳርጓል:: ይህን ግጭት ለማርገብ ወታደራዊ እርምጃ ተወስዶ ስለነበር ከሁሉም ወገን በሚሰነዘር ተኩስ ሕይወት ጠፍቷል፣ የአካባቢው ሰላም ተናግቷል፣ ከብቶች ተዘርፈዋል፣ እህልና ቤት ተቃጥሏል፣ ከሁሉም በላይ 12000 (አስራ ሁለት ሺህ) ያህል ሰፋሪዎች ለዳግም ስደት ተዳርገዋል:: ይህ ጥናት በተካሄደበት ጊዜ ተፈናቃዮቹ በአዊ ዞን በሚገኘው ዳንግላ ወረዳ ጃዊ ቀጠና ላይ በተዘጋጀላቸው 265,281 ሔክታር መሬት ላይ በመልሶ ሰፈራ ሒደት ውስጥ ነበሩ::

የተሰባሰቡ መረጃዎችን መሰረት በማድረግ ጥናቱ መሠረታዊ የሆኑ የግጭቱ መንስኤዎችን በሚከተለው ሁኔታ አስቀምጧቸዋል::

### *ሀ) በአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት መመናመን*

የጥናቱ ውጤት እንዳሳየው ሰፋሪዎቹ ለእርሻ መሬትነት ያዋሏቸው ቦታዎች ደኖችን በመጨፍጨፍ ነው:: ይህ ደግሞ የአካባቢ መራቆትንና የአየር ንብረት መዛባትን በማስከተሉ ለግጭቱ ቀጥታ መንስኤ ሆኗል:: በአካባቢው በልምድ የተፈጥሮ ሀብትን ለመንከባከብ ይደረግ የነበረው ሙከራም በሕዝብ ብዛት ጫና እያደገ በመጣው የመሬት ፍላጎት እየተለወጠ በመምጣቱ መሬቱ የደን ሽፋኑን ማጣቱ ብቻ ሳይሆን ለምነቱም እየቀነሰ እንደሄዴ የአካባቢው ነዋሪዎችና ባለሥልጣናት በአንክሮ ይናገራሉ::

### *ለ) ፖለቲካዊ ምክንያቶች*

አንደኛውና ዋነኛው ፖለቲካዊ ምክንያት እ.ኤ.አ. በ1991 ዓ.ም. በሀገሪቱ የተካሄደው የመንግስት ለውጥ የሽግግር

መንግስት ምስረታውና በ1994 የተረቀቀው ሕገ መንግስት ሒደት ዋነኛ መሠረቶች የፖለቲካ ችግሮችን ለመፍታት የብሔር ብሔረሰቦች ዕኩልነት የሚረጋገጥበትን ሥርዓት መመስረት እንደነበር ይታወሳል። በዚህም ምክንያት የፌደራላዊ ሥርዓት አወቃቀሩ በጎሳ ላይ መመስረት በአንዳንድ ቦታዎች አጎራባች ድንበሮች እንደገና እንዲከለሉ በነበረው ፍላጎት የይገባኛል ግጭት ወይም የብዙሀን-አናሳ ግንኙነት መሻከርንና ግጭትን ማስከተሉ አልቀረም። ቀደም ሲል የተጠኑ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ጊዳ ኪረሙ ወረዳ ላይ በአማራ ሰፋሪዎችና ኦሮሞ ተወላጆች መካከል ለተፈጠረውም ግጭት ይኸው አስተሳሰብ የራሱ ሚና እንደነበረው ተጠቁሟል።

ሰፋሪዎቹ የአካባቢው ተወላጆች ያለመሆናቸው በተለይም አካባቢውን አልምተው የተፈጥሮ ሀብቱን ተጠቅመው ኑሯቸውን ማሻሻላቸው በየትኛውም በጎሳ ላይ የተመሰረተ አስተሳሰብ ባለበት ሕብረተብ ውስጥ ሁሉ ሊፈጠር የሚችለውን አይነት ቅሬታ መፍጠሩ የማይቀር ነው። በጊዳ ኪረሙ ሰፍረው የነበሩና አሁንም እዛው ያሉ አማሮች ነበር ብለው የሚገልፁት ፀረ-ሰፋሪ ቅስቀሳም መሰረቱ ይኸው ነው። ሰፋሪዎቹ ለደረሰባቸው መፈናቀል በጎሳ ላይ የተመሠረተ ቅስቀሳና ማግለል መሆኑን ያምናሉ። ለዚህም በዋናነት የሚጠቅሱት የአካባቢው ሚሊሺያ፣ አስተዳደርና ኃላፊዎችን ሚና ነው።

ሁለተኛው ፖለቲካዊ ምክንያት አማሮቹ የሰፈሩባቸውን ቦታዎች የሚያካልል ልዩ "የአማራ ዞን" እንዲፈጠር ይፈልጋሉ የሚለው ድምዳሜ ነው። ሠፋሪዎቹ ይህንን የጠየቁበት ሁኔታ ሊረጋገጥ አልቻለም። ነገር ግን የተለያዩ ነባር ቦታዎችን ስም ከደብር ስም ጋር በማያያዝ በአማርኛ መጥራት፣ በአካባቢው የሌለ የወረዳ ስም በመፍጠር "የጉተን ወረዳ አብያተ ክርስትያናት ማህበር" በሚል መጠርያ 17 ቤተክርስትያናትን ያቀፈ ማህበር ማሰባሰብና በአብዛኛው ሰፋሪው እርስ በእርሱ ያለው መተባበርና ትስስር እየጎላ መምጣት ሌላው የግጭት አቀጣጣይ ምክንያት ሆኗል።

ሦስተኛው ፖለቲካዊ ምክንያት የሀገሪቱ በጎሳ ላይ የተመሠረተ ፌደራላዊ አወቃቀር አካል የሆነው ከ1984 ጀምሮ ሰፋሪዎቹ በአካባቢው አስተዳደር እንዳይገቡ መደረጉ ነው። የመስሪያ ቋንቋውና ጎሳ ከግምት በመግባታቸው ከተወላጆች መካከል በስሜታዊነት ሰፋሪዎችን ማግለል ለሚፈልጉት በር የከፈተ ሲሆን ሰፋሪዎቹም እራሳቸውን ነጥለው እንዲመለከቱ አስተዋፅኦ አድርጓል ።

### *ሐ) ማህበራዊና ባህላዊ ምክንያቶች*

ሰፋሪዎቹ የራሳቸውን አካባቢ የተለየ ስም ለመስጠት ያደረጓቸው እንቅስቃሴዎችና የአካባቢውን ቋንቋ ለመልመድ ብዙም ያለመጨነቃቸው የሚያሳየው ሰፋሪዎቹ የሚኖሩበትን ህብረተሰብ ወግ ባህልና ቋንቋ አክብሮ ለመኖር ያሳዩት ጥረት አናሳ መሆኑ ተስተውሏል። የቦታ ስሞችን ቀይሮ በአማርኛ ስሞች የመተካት ሒደት የሚያሳየው ይህንኑ ነው። ለአብነት ያህል 'አሮ' ተብሎ ይጠራ የነበረውን አካባቢ 'ሐሮ አዲስ አለም'፣ 'አጃና' ይባል የነበረውን የቦታ ስያሜ 'አዛና ስላሴ'፣ 'አሮ ባጊን' ይባል የነበረው ቦታ 'ባጊን ማርያም' እና ሌሎችም አነስተኛ የስም ለውጦች የአካባቢውን ተወላጆች ሊያስቆጣ መቻሉ እውን ነው።

ሁለተኛውና አሁንም በማህበረሰባዊና ባህላዊ ጉዳዩች ውስጥ ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ምክክር ሳይደረግና የጋራ መግባባት ሳይፈጠር ቤተክርስትያናትን ማነፅ በአካባቢው ለተፈጠረው ግጭት ሌላ ምክንያት መሆኑ አልቀረም። ሠፋሪዎቹ የአካባቢውን ተወላጆች ሳያማክሩ ቤተክርስቲያናትን መገንባታቸው ቅሬታን አሳድሯል።

### *መ) የትምክህት ባህሪና ተፅዕኖው*

የትኛውም የጎሳ ሥርዓትና ባህል ለዚያ ጎሳ ብቻ ሳይሆን ለሀገርም ክብር ነው። ይህ በአንዳንድ ሰፋሪዎች ዘንድ ግንዛቤ ባለማግኘቱ የሚሰነዘሩ የትምክህት ፌሊጣዊ አነጋገሮች ወደ ስሜታዊነት እንዳመሩ ይህም ጥናቱ በተካሄደበት አካባቢ አንድ የግጭት መንስኤ እንደሆነ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሁሉ በአፅዕኖት ይናገራሉ። በፊውዳላዊው ሥርዓት ውስጥ የነበሩ የታሪክ አሻራዎች ዛሬም በተለያየ መልኩ በሚነሱበት የፖለቲካ ሒደት ውስጥ እንዲህ አይነት ጉዳዮች ግጭትን ለመቀስቀስ አስተዋፅዖ አላቸው።

### *ሠ) ሕግና አስተዳደራዊ ምክንያቶች*

አንደኛ ሰፋሪዎቹ ወደ ወረዳው ሲገቡ በግዢና በኮንትራት ውል መሬት ይዘው የቆዩ ሲሆን ውሉ ሲያድር የአካባቢው ተወላጆች ወይም የአንድ ቤተሰብ አባላት በመሬቱ ኮንትራትና ግዢ ውል አግባብ ያለመሆን ላይ የሚያነሱት ክርክር ነው። ይህንን ተከትሎ ፍርድ ቤቶች መሬት ለባለቤቱ እንዲመለስ ወይም ሰፋሪዎቹ እንደገና እንዲከፍሉ ሲበይኑ በሰፋሪው በኩል ውሳኔውን ባለመቀበል ከፖሊስና ከሚሊሺያ ጋር የሚጋጩበት ሁኔታ ተከስቷል።

ሁለተኛ ሰፋሪዎች ትጥቅ እንዳይዙና ህጋዊም ከሆኑ እንዲያስመዘግቡ ሲጠየቁ ፈቃደኛ ያለመሆናቸው በሌላ በኩልም ከ1987 ዓ.ም. ወዲህ የሰፈሩት በወረዳ የገጠር ቀበሌ አስተዳደሮች ለመመዝገብ ያለመፍቀዳቸው ተጨማሪ ምክንያቶች ሆነዋል። በሰፋሪዎቹ የሚገለጸው ግን የመሳርያ ማስረከብ ጉዳይ እነሱ ብቻ ተለይተው እንደተጠየቁና ምዝገባውም እነሱን በህገ ወጥነት ፈርጆ ከቦታው ለማስወጣት ነው በሚል ስጋት ለመመዝገብ ያለመፍቀዳቸውን ይናገራሉ።

ሌላው ለግጭቱ መባባስ ምክንያት ከሆኑት ጉዳዮች መካከል አንዱ በሁለቱም ጎሳዎች መካከል ይካሄድ የነበረው ከብቶችን የመዝረፍ ድርጊት ነው። በተለይም በሰፋሪዎቹ በኩል የሚነገረውና ጉዳዩን ዕልባት እንዲሰጥ ይጠበቅበት የነበረው የፖሊስና የፍትህ አካላት ዕልባት ያለመስጠት ሁሉም ወገን ራሱን ወደሚከላከልበት አቅጣጫ እንዲያመራ የገፋው ይመስላል። ሰፋሪዎቹ መሣርያ ለመታጠቃቸው የሚሠጡት ምክንያትም ይህንን ነው። በዚህ ዓይነት ግጭት ለጠፋ ህይወት ተጠያቂ የሆኑ ወንጀለኞችን ለሕግ አሳልፎ ባለመስጠትም ሰፋሪዎቹ የሚወቀሱበት ጉዳይ መሆኑን የአካባቢው የመንግስት ኃላፊዎች ይገልፃሉ።

### *ረ) ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች*

የአካባቢው መሬት ያለማቋረጥ ለሚመጡ አዳዲስ ሰፋሪዎች በኮንትራትና በተለያዩ መንገዶች በተሰጠ ቁጥር ለሚከሰተው የመሬት ጥበትና እጦት ምክንያት ነዋሪዎች ለልጆቻቸው የሚተውት ቅሪት አይኖርም። ይህ ደግሞ ወጣቱን መሬት አልባ ከማድረግ አኳያ አስተዋፅኦ እንዳለው ተስተውሏል።

### **5. ማጠቃለያ:-**

በዚህ ጥናት ለሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ ተጋላጭነት፣ ፍልሰት፣ ሰፈራና ግጭት መካከል ያሉትን ግንኙነቶች ለማሳየት ተሞክሯል። ከአካባቢ ሁኔታ ፖለቲካዊ፣ አኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ህጋዊና ባህላዊ መነሻ ባላቸው

ምክንያቶች ከትውልድ ሥፍራ መፍለስ ያለውን ያህል ተመሳሳይ መነሻ ባላቸው ምክንያቶች ዳግም መፈናቀልንና መልሶ ሰፈራን በሚያስከትል አዙሪት ውስጥ የሚገባበት ሁኔታ እንዳለ ተመልክቷል::

እንዲህ ባለው ትስስር አሉታዊ ውጤቶች የሚደርሰው የኑሮ መመሳቀል በቀጥታ በጉዳዩ ውስጥ የተገኙትን ብቻ ሳይሆን ጉዳቱን ለማስተካከል በሚወሰድ እርምጃ የሀገር ሀብትና በመልሶ ማስፈር ሒደት ሌሎች አካባቢዎችም ላይ ጫና መደረጉ አይቀርም:: ለምሳሌ ከጊዳ ኪረሙ የተፈናቀሉትን 12000 ሰዎች መልሶ ለማስፈር ከግንቦት 1993 እስከ ጥቅምት 1995 ባለው ጊዜ ውስጥ ከሦስት ሚሊዮን በላይ ወጪ ሆኗል:: ተፈናቃዮቹ አዲስ ቦታ እንዲሰፍሩ ፈቃዳቸው የነበረ ቢሆንም የመሬቱ ለእርሻ ምቹ ያለመሆንና የአንዳንድ እንደ ጤና አገልግሎቶችን ያለመሟላት የተፈናቃዮቹ ኑሮ በአጭር ግዜ የሚረጋጋ እንዳልሆነ የሚገልጹ ሲሆን በአጥኚው ዕይታም ጊዜ የሚወስዱና ተጨማሪ ጥረቶችን የሚፈልጉ ጉዳዮች እንዳሉ ተስተውሏል:: ከዚህም በላይ በገንዘብ የማይተመነው የሰው ልጅ ሕይወት የኑሮ መመሳቀልን ተከትሎ የሚፈጠረው የሥነልቦና መላሸቅ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ከምንም በላይ የሚያሳስቡ በመሆናቸው የሚከተሉት የፖሊስ ሀሳቦች ተጠቁመዋል ::

### ለፖሊሲ ሀሳቡ መነሻ የሆኑ ነጥቦች:-

ሀ) በሀገሪቱ ውስጥ ሰዎች እጅግ ከተጎዱና ለኑሮ አመቺ ካልሆኑና ከተራቆቱ አካባቢዎች እንዲለቁና ወደ ሌሎች የተሻሉ አካባቢዎች የሚሰፍሩበት ሒደት ሁሌም የሚኖር መሆኑ፣

ለ) በራስ ፍላጎትም ቢሆን የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ሰዎች ከትውልድ ስፍራ እየለቀቁ ስለሚሄዱና መንቀሳቀስም ህገ መንግስታዊ መብታቸው ስለሆነ መገደብም ስለማይቻል፣ ነገር ግን ተመሳሳይ ችግር እንዳይፈጠር ትምህርት መውሰድ የሚያስፈልግ በመሆኑ፣

ሐ) በተለይ በጥናቱ አካባቢ አሁንም ከ18000 በላይ ሰፋሪ አማሮች በመኖራቸው ምናልባት ላለፈው ግጭት መንስዔ የሆኑ ጉዳዮች እንዳያገረሹ ችግር ቢፈጠርም ባግባቡ ለማስተናገድ እንዲያመችና ከዚህ የተገኘውን ትምህርት በገንቢ መልኩ መጠቀም እንዲቻል ነው::

### ጠቋሚ ሀሳቦች:-

- ግጭቶች ባግባቡ ከማይፈቱባቸውና እንደገናም ሲያገረሹ ከሚታይባቸው ምክንያቶች ዋናዎቹ በጉዳዩ ላይ በግልፅ ያለመነጋገር፣ መሸፋፈንና ዋናውን ምክንያት ወደ ጎን በመተው ምልክቶችን ማስታመም ናቸው:: በግጭት ውስጥ የገቡ ወገኖች መንስኤዎችን ለይተው በግልፅ እንዲወያዩ ኃላፊነት ያለበት ሁሉ በዚሁ መልክ ግጼታውን መወጣት እንዲችል ማድረግ፤
- የልማት ስትራቴጂዎች ፍልሰትን የሚቀንሱ፣ ቢቻል የማያስከትሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ ቢቻልም የአደጋ ተጋላጭነት ሲፈጠር ህብረተሰቡ በአካባቢው ያለውን አማራጭ ሁሉ እንዲጠቀም የሚረዳ የአሠራር ስርዓት መዘርጋት፤
- ሠፈራ እንደ አንድ አማራጭ ከተወሰደም መልሶ የማስፈር ሂደቱ የሠፈራ ቦታዎችን የተፈጥሮ ሀብትና ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮችን ከግምት ያስገባ እንዲሆን ማድረግ፤
- በፌደራላዊ አወቃቀር ውስጥ በጎሳ ላይ የተመሠረቱ ጥላቻዎችና የማናናቅ ቅስቀሳዎች አንዱን ከሌላው ከፍ ወይም ዝቅ አድርጎ የሚያሳይ አመለካከት፣ ወዘተ እንዳይፈጠር የሚያደርግ የፖለቲካ አቅጣጫ ላይ ማተኮርና እስከአሁን የተፈጠሩ ግጭቶችን መንስኤም በአግባቡ ማጥናት እንዲሁም ልምዶችን መመዝገብ፤
- በኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝቡ በአብሮ መኖር ልምዱ ላካበተው ትስስሩ ዋቤ የሆኑ የግጭት አፈታት ዘዴዎች ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ፣ ለምሳሌ የጋራ የሠላም ኮሚቴዎችን በማቋቋም የንግግር ባህልን ማዳበር፤
- በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ሕገ-መንግሥት መሰረት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በየትኛውም የሀገሪቱ ክልል ውስጥ የመኖር፣ የመስራትና ራስን በማስተዳደር ሂደት ውስጥ የመሳተፍ መብት እንዳለው ስለሚያረጋግጥ በዚሁ መሰረት ሰፋሪዎችና ተፈናቃዮች ባሉበት አካባቢ ውስጥ ይህ መብታቸው እንዲከበር::

ተስፋዬ ታፈሰ (ዶ/ር)

**ምንጭ:-** 1. Tesfaye Tafesse. The Migration, Environment, Conflict Nexus. FSS Studies on Poverty, No. 4, 2004.
2. Tesfaye Tafesse. *The Migration Environment and Conflict Nexus in Ethiopia: A Case Study of Amhara Migrant-Settlers in East Wollega Zone.* OSSREA, 2007.

**Acknowledgement & Disclaimer**

*This document has been produced with the financial assistance of the European Union. The contents of this document are the sole responsibility of the author and can under no circumstances be regarded as reflecting the position of the European Union.*

አድራሻ: የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ♦ ፖ.ሳ.ቁ 25864 ኮድ 1000 ♦ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
ስልክ: 011-157 29 90/91 ♦ ፋክስ: 011-157 29 79
ኢሜይል: fss@ethionet.et ♦ ድረ ገፅ: www.fssethiopia.org.et